# ያልታደሉቱ !!

**አትናቲዎስ**

09-19-14

ያልታደሉና የታደሉት የሚባል አባባል በሀገራችን አለ፡፡ በብዙ የሕይወት ተፋሰሶች ከፍታዎች፤ ጥጋ ጥጎች፤ ሰርጥና ሸለቆዎች ውስጥ ይከሰታል፤ ይመጣል፤ ይሄዳል፡፡ በየዘመኑ ፈረቃ ይነሳል፤ ይደገማል፡፡ ይቀጥላል፡፡ ያልታደሉቱ በእድለ ወድቀት ፈተና፤በማይሳካው የህይወት ጉዞና ውጣ ውረድ መንከባለል፤ መፍገምገም ውስጥ የሚኖሩትን ያለፉትን ሲያካትት፤ የታደሉቱ በስኬት በመላቅ በከፍታ ጉዞና እርምጃ ችግሮችን እንደ ብጤታቸው መላ እያበጁላቸው መሰናክሉን በፈተና እያለፉ ጉዞውን በአሸናፊነት የሚራመዱትን ይገልጻል፡፡

ግለሰብም፣ ቤተሰብም፣ ትውልድም፣ ሀገርም በሁለቱም ውስጥ ይሽከረከራሉ፤ ያልፋሉ፤ ከሁለት ባንዱም ይጠቀሳሉ፡፡ ባልታደሉት ወይንም በታደሉቱ፡፡ ወይንም በሁለቱ፡፡ የፅሁፉ ነገረ መነሻ ትኩረት እንዳሻቸው ትውልዱንም ሕዝቡንም ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ የሚነችፉትን፤ በስድብና በዘለፋ የሚሸነቁጡትን፤ የሚያብጠለጥሉትን፤ማዕረጉን በዚህ ያገኙ የሚመስሉትን ፕሮፌሰር መሥፍን ወልደማርያምን ይመለከታል፡፡፡

ከሸገር ኤፍኤም ራዲዮ የቅዳሜ ከሰዓት ፕሮግራም ከመዓዛ ብሩ ጋር ለተከታታይ ሣምንታት ከግለ ህይወት እስከ ሥራና ኃላፊነት እንዲሁም በሦስቱ መንግሥታት ውስጥ ስላሳለፉትና ስለነበረው ስላለው ፖለቲካም ጭምር ፕሮፌሰር መሥፍን ወልደማርያም ሞልቶ ከተትረፈረፈው ስድብና ዘለፋቸው ውጪ የራሴ የሚሉትን አስተሳሰብ በሰፊው አስደምጠዋል፡፡

ፕሮፌሰር መሥፍን ወልደማርያም የኖሩበትና የተራመዱበት ሕይወትና ጎዳና የተመሰቃቀለና  የእርሳቸውም ስብዕና እንዲሁ ውስብስብ ነው፡፡ ሁሉን ነገር በመቃወም ያምናሉ፤ መቃወምና መተቸት በቅጡና በተገቢው መንገድ ቢሆን ከስህተት ለመማር ከውድቀት ለመታደግ ይረዳል፡፡

በተለይም ደግሞ በእድሜ የገፉ አዛውንት ኢትዮጵያውያን ምሁራን ተተኪ ለሆነው ወጣት ትውልድ ኢትዮጵያዊ ባሕልና ጨዋነትን ማስተማር፤ የተለያዩ ብሄር ብሄረሰቦች ባሕል ቋንቋ እምነት ያለባት ሀገር እንደመሆኗ መጠን ተቻችሎና ተግባብቶ መኖር አስተዋይነትና ስክነትን መቻቻልን መከባበርና መደማመጥን እንደ አባት ማስተማር ትውልዱን በአብሮነት መንፈስና በእውቀት የመቅረፅ አባታዊ ኃላፊትና ግዴታ አለባቸው፡፡

ይኼ ምሁራዊና አባታዊ አደራና ቀድሞ የነበሩት ችግሮች እንዳይገደሙ፤ የእርስ በእርስ ግጭት እንዳይፈጠር፤ የሀገሪቷ ዜጐች የእኩልነት መብት በሁሉም መስክ የተከበረባት ሁሉም በጋራ በሠላምና በደስታ ተከባብሮ የሚኖርባትና የሚያሳድጋት ሀገር እንድትሆን የየበኩላቸውን ድርሻ መወጣት ይገባቸዋል እንጂ ወደ ከፋ ሁኔታ የሚወስዱ መንገዶችን መሪና ጠቋሚ መሆን የለባቸውም፡፡

ሁሉም አዛውንትና ጎምቱ ወይንም አንጋፋ ምሁራን ተተኪው ትውልድ ሀገሪቱን ጠብቆና አልምቶ አሳድጎ እንዲራመድ እንጂ ሀገሪቷን ምስቅልቅል ፖለቲካና ትርምስ ውስጥ እንዲከታት አይፈቅዱም፤ አይፈልጉምም፡፡ ጥቂቶች አዛውንት ምሁራን ፕሮፌሰር መሥፍንን የመሰሉት ሀገርቷ በሠላማዊ መንገድ በሠላማዊ ምርጫ በሠላም የጀመረችውን የልማት ጉዞ መቀጠሉን አይቀበሉትም፡፡ በፕሮፌሰር መሥፍንና በመሰሎቻቸው አመለካከት ዛሬ በሀገሪቱ ያለውን ሠላምና ዓለም የመሰከረለትን ታላቅ የኢኮኖሚ እድገት ያጣጥሉታል፤ የለም ብለው እስከማለት ይደርሳሉ፡፡

መሠረቱ ስለተጣለ የጐደለው እየሞላ ጥራቱና ብቃቱ በጊዜ ሂደት እየጐለበተ ይሄዳል፡፡ የዩኒቨርስቲዎች፤ የኮሌጆች፤ የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃና የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፤ የግልም የመንግሥትም ከዚህ ቀደም ባልታዩ ሁኔታ ተስፋፍተዋል፡፡

ለትምህርትና ለጤና መስፋፋት የተሰጠው ልዩ ትኩረት፤ ለመሠረተ ልማት ግንባታ መስፋፋት የመንገዶች፤ የቤቶች፤ የግድቦች፤ የተለያዩ ሕዝባዊ አገልግሎቶች የሚሰጡና ሕዝቡን ተጠቃሚ የሚያደርጉ ሥራዎች መሰራታቸውን የአባይን ግድብ ግንባታ ጨምሮ እነ ፕሮፌሰር መሥፍን ዓይናቸው እያየም ከማጥላላትና ከማንቋሸሽ

ምንም እንዳልተሰራ አድርገው በስሜታዊነት የተሞላ የጥላቻ ፕሮፖጋንዳ ከማካሄድ ለአንዲት ቀን ተግ ብለው አያውቁም፡፡ መልካም ለማሰብ ያልታደሉ የመርገምት ውልዶች ናቸው፡፡

የፕሮፌሰር መሥፍን ምስቅልቅና በውስጠ ተቃርኖ የተመላ ስብዕና ሁሉንም መቃወምና ማጥላላት፤ ከእኔ በላይ አዋቂ የለም ማለት ከንጉሱ ዘመን እስከ ዛሬ የዘለቀ በመሆኑ ለብዙዎች እንግዳ አይደለም፡፡ አብረው የሰሩና የሚያውቋቸው ሰዎች የገለሰቡን ሞገደኛና ነውጠኛ ቡጢ አፍቃሪ ባሕርይ ጭምር ያስታውሳሉ፡፡ ይህ አስነዋሪ ግለ ባሕርይ ሀገራዊ ፖለቲካዊ ውስጥ ገብቶና ነፍስ ዘርቶ ብዙ ተተኪ ነውጠኛ መሥፍኖችንም እንደ መርህ የቀረፁበት ሁኔታ ትናንትም ዛሬም እየታየ ነው፡፡

መርህ ይከበር በሚል በፕሮፌሰር መሥፍን የሚመራውና ከአንድነት ተገንጥሎ የወጣው ቡድን (የዛሬው ሰማያዊ ፓርቲ) የአንድነት ቢሮን በይገባኛል ለመቆጣጠር የሞከሩት በሰለጠነ ፖለቲካና በውይይት፣ በመነጋገርና በመግባባት አልነበረም፡፡ ይልቁን በቦክስና በድንጋይ በዱላ ነበር፡፡ መሀል ላይ ፖሊስ ገባ፡፡ ችግሩን አበረደው፡፡ ያ ባይሆን ኖሮ ብዙ ደም ይፋሰስ ነበር፡፡ እንግዲህ እነ ፕሮፌሰር መሥፍን አዛወንቶቹ ምሁራን ተቃዋሚ ፓርቲ ነን ነገ እድሉን ካገኘን ሀገርና ሕዝብ ለመምራት ብቁ ነን እያሉ አሥሬ ለሕዝቡ በየአጋጣሚው የሚለፍፉት እነዚህ ወይንም እንደዚህ ናቸው፡፡

በአጭሩ ሥልጣን ላይ ሁሉም አቅም ኖሯቸው ያሉ ቢሆኑ ደግሞ ለተቃረናቸው፣ ለተቃወማቸው የሚሰጡት ምላሽ ቦክስ ሳይሆን ያለጥርጥር በጥይት ከመፍጀት እንደማይመለሱ ይኸው ትንሹ የማንነታቸው ምስክር የሆነው ተግባራቸው በቂ ማረጋገጫ ነው፡፡ ይህ ያላቸውን ፍፁም ፀረ ዴሞክራሲ የሆነ ጭፍን አምባገነናዊ ግለሰባዊም ሆነ ድርጅታዊ ባሕርያቸውን ያሳያል፡፡ ዴሞክራቶች ነን ቢሉም ላለመሆናቸው በርካታ ማረጋገጫዎች አሉ፡፡

ፕሮፌሰር መሥፍን እስከ አሁኑ የ81 ዓመት እድሜያቸው ድረስ በኢትዮጵያ ያለፉትን ሁለት የቀድሞ ሥርዓቶች የንጉሱንና የደርግን ዛሬም ያለውን መንግሥት ለማየት የቻሉ በውስጣቸውም ያለፉበትና አሁንም ኖረው እየተመለከቱ ነው፡፡

ትናንት የነበረችው ኢትዮጵያ ምን ትመስል እንደነበር ያውቃሉ፡፡ ዛሬ በእርግጥ በተጨባጭ በሚታይ ደረጃ ያውም ሥር ነቀል የሚባል ለውጥ አለ፡፡ የእያንዳንዱ ብሄር፣ ብሄረሰብና ሕዝብ መብት ባሕሉ፣ ኃይማኖቱ ቋንቋው ተከብሯል፡፡

ከዚህ በፊት በነበሩት ሥርዓቶች ያልነበረ ፕሮፌሰር መሥፍንም እንዳሻቸው ሲላቸው በየስብሰባው፣ በራዲዮው፣ በየመጽሔቱና በየጋዜጣው ያለገደብና በነጻነት፤ ሲላቸውም እየተሳደቡ፣ እየዘለፉ ጭምር ሀሳባቸውን የመግለጽ መብታቸው፤ የፕሬስ፣ የመናገርና የመደራጀት ነፃነት አልተከበረም ሲሉ ሊያፍሩ ይገባቸዋል፡፡ በመድበል ፓርቲ ሥርዓት አካሄድ ከዚህ በፊት በሀገሪቱ ባልነበረ ሁኔታ የተለያዩ ተቃዋሚ ፓርቲዎች የየራሳቸው ጠንካራና ደካማ ጐን እንዳለ ሆኖ በነፃነት ተደራጅተዋል፤ ቢሮ ከፍተዋል፡፡ተቃውሚቸውን ያስማሉ፤ ለምርጫም ይወዳደራሉ፡፡

ፕሮፌሰር መሥፍን በመሠረቱት ቀስተ ደመና ፓርቲ ይህን ይዘው በ1997 ቅንጅትን ተቀላቅለውም መርተዋል፡፡ ከቅንጅት መበታተን በኋላ አንድነት ፓርቲን በልዩነት ለቀው እስከወጡ ድረስ ሲሰሩ ቆይተው በመርህ ይከበር ልዩነት ለቀው የዛሬውን ሰማያዊ ፓርቲ ከጀርባ ሆነው መሥርተው ዛሬም ተቃውሚቸውን እያካሄዱ ነው፡፡ መብታቸው የተከበረ ነው፡፡

ፕሮፌሰር መሥፍን ከትናንት እስከ ዛሬ የኖሩባት ኢትዮጵያ አይደለም ተወላጅ ዜጐች ሌሎችም የውጪ ሰዎችና ተቋማት ሀገሪቷ በፈጣን ልማትና እድገት ላይ መሆኗን ደጋግመው መስክረዋል፤ እየመሰከሩም ነው፡፡

እሱና እነሱ ያሉት፣ ያሰቡት፣ ያመኑበት ካልሆነ በስተቀር የሌሎችን የተለየ ሀሳብ በልዩነት መቀበል ቀርቶ መስማትም ማዳመጥም አይፈልጉም፡፡ ይህም ብቻ አይደለም፡፡ ለኢትዮጵያ እውነተኛ አሳቢዎች፣ ተቆርቋሪዎች እኛና እኛ ብቻ ነን ባይ ናቸው፡፡

የሌላውን ወገን አስተሳሰብና አመለካከት ዜግነት ክብር የሚረገጥ የሚደፈጥጥ ብሎም በጠላትነት የሚፈርጅ ኋላ ቀር የሆነ የጨለማ ፖለቲካ ውስጥ ሰምጠው ተተኪው ትውልድም ይህንኑ የእብሪተኛ የአምባገነነት የጥላቻ የስሜታዊነት ባሕርያቸውን እንደ መልካም ነገር እንዲወርስ ማድረግ ችለዋል፡፡ ትናንትም እንዲህ ነበሩ፤ ዛሬም በዚሁ ቀጥለዋል፡፡

ፕሮፌሰር መሥፍን በንጉሱም ሆነ በደርግ ዘመን እንዲህ እንደ አሁኑ ነውረኛና ለሀገርና ለትውልድ የማይበጅ አስተሳሰባቸውንና አፍጥጦ የወጣ የሥልጣን ናፋቂነት ጥማቸውን በተለያየ ጭምብል የማራመድ እድሉ አልነበራቸውም፡፡ እሳቸውም ይህን ጠንቅቀው ስለሚያውቁ ኮሽታ ሳያሰሙ ኖረዋል፡፡ እንደ አሁኑ በማን አለብኝነት ተነስተው አገር ምድሩን ሕዝቡን ትውልዱንም ልዝለፍ፣ ልሳደብ ቢሉ ቀጣዩን ነገር ያውቁት ስለነበር ተሰብስበው ኖረዋል፡፡ በእሳቸው እምነት ይህንንም የተገኘ የዴሞክራሲ መብት እንደ ልብ እየተጠቀሙበትም የለም ብለው የሚክዱ መሆናቸውም በራሱ ያስገርማል፡፡ ፕሮፌሰር መሥፍን ከንጉሰ ነገሥቱ መንግሥት መውድቅ በኋላ ደርግ ባቋቋመው አጣሪ ኮምሲዩን ውስጥ አባል ሆነው ሲሰሩ እነዚህን ከፍተኛ ባለሥልጣናት አሥራችሁ የምትቀልቡት ለምንድነው? የሚል ጥያቄ ለደርግ ማቅረባቸውን ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም አልሸሸጉትም፡ በንጉሱ ሚኒስትሮች ላይ እርምጃ እንዲወሰድ ትልቅ ግፊት ያደርጉ እንደነበረም ገልፀዋል፤ ፕሮፌሰሩ ግን ይክዳሉ፡፡ እሱን አትስሙት እብድ ነው ይላሉ፡፡ በራሳቸው በፕሮፌሰር መሥፍን ቋንቋ ራሳቸው በክህደትና ሸፍጥ የተሞሉ በላኤ ሰብ ናቸው ማለት ነው፡፡ በግዕዙ ሰው በላ እንደ ማለት ነው፡፡

እንደገናም ፕሮፌሰር መሥፍን ከምዕራባውያን መንግሥታት ኤምባሲዎችና ተቋማት ጋር ባላቸው ጥብቅ ትስስርና ግንኙነት የራሳቸውን አተያይና መረጃ እንደሚያካፍሏቸው የመጀመሪያ ደረጃ ታማኝ የመረጃ ምንጭ ተደርገው ይወሰዱ እንደነበር  ይታወቃል፡፡ ይህንንም ልዩ ግንኙነት በመጠቀም ነው በዓለም አቀፍ የኒዮ ሊበራል አክራሪ ደጋፊ በሆነው የኒዮ ሊበራሉ አክራሪ ከበርቴ ጆርጅ ሶሮስ ቀጥታ ድጋፍ ከሚተደደሩት ዓለም አቀፋዊ ስመ ብዙ ተቋማት አንዱ ከሆነው አምነስቲ ኢንተርናሽናል ጋር በመምከር የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ጉባዔን (ኢሰመጉን) መሥርተው በፍፁም አምባገነንነት ለዓመታት የመሩት፤ በኋላም የለቀቁት፡፡

የድርጅቱ መቋቋምና ሊሰሩበት የተንቀሳቀሱት የጀርባ ዓላማ ምን ነበር? የሚለው ነው አነጋጋሪው፡፡ ይህም የተቃውሞ ፖለቲካውን ለማጋጋምና በምዕራቡ ዓለም ድጋፍና ተቀባይነት እንዲያገኝ፣ እርዳታም እንዲሰጠው በማድረግ የተቃዋሚ ኃይሉ

ተቀባይነት እንዲያገኝ የሄዱበት መንገድ ነው፤ በብዙ ሚሊዮን ዶላር እርዳታ ከውጭ አግኝተውበታል፡፡

ይህ ከውጪ መንግሥታትና ተቋማት ለእነ ፕሮፌሰር መሥፍን በገፍ ሲፈስና ሲገባ የነበረው ዶላር ለኢሰመጉ ቢሮ ኪራይና ለሠራተኛ ደመወዝ፣ ለቅርንጫፍ ተጠሪ ቢሮዎች ወጪ፣ ለወርክሾፕና ስብሰባ፣ ለሚያሳትሙት ጋዜጣ፣ ለትራንስፖርት፣ ለሥራ ማስኬጃ፣ ለስልክ፣ ለፋክስ፣ ለውሎ አበል ከሚባለው እዚህ ግባ የማይባል ወጪ በላይ የገዘፈ ነው፤ ኢሰመጉ እስከታገደበት ጊዜ ድረስ ከፍተኛ ገንዘብ በባንክ አካውንቱ ውስጥ ነበረው፡፡ ምን ሊሰራበት ነበር የታቀደው የሚለው መልስ የለውም፡፡

ሰብዓዊ መብት እንዲከበር ማስተማርና ማሳወቅ ዜጐች የሕጋዊ መብቶቻቸው ሕጋዊ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማበረታታት፤ ሕገ ወጥ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን ማጋለጥ፤ በተጨባጭ በደል የተፈፀመባቸውን ፍርድና ፍትህ ያጡ ዜጐችን ማሳወቅ ተገቢ ሥራ ሲሆን ጠቃሚነቱ ለመንግሥትም ለሕዝብም ነው፡፡ በታዳጊ ዴሞክራሲና የደረጀ የፖለቲካና የዴሞክራሲ ባህል በሌለበት ሀገር ብዙ ችግሮች በዜጐች ላይ ሊፈጠሩ ይችላሉ፡፡ ይህም ከሕግ አስፈፃሚ ግለሰቦች በቂ እውቀትና ግንዛቤ ማጣት የሚፈጠር በመሆኑ ለማረምና ለማስተካከል ይጠቅማል፡፡

መንግሥት ደረጃ በደረጃ የታዩ ስህተቶችን፣ ጉድለቶችን የሰብዓዊ መብት ጥሰትን፣ የመልካም አስተዳደርና የፍትሕ እጦት መጓደል ችግሮችን ከሥሩ በመከታተል የእርምት እርምጃ ወስዶ እየሰራ በመሆኑ ትርጉም ያለው ለውጦችን ማምጣት ችሏል፡፡ ሥራው በጊዜ ሂደት የማቀጥል እንጂ የሚቆም ባለመሆኑ የማረሙና የማስተካከሉ ሂደትም ይቀጥላል፡፡

ይህ መልካም ቅንነት እያለ ተሰርቶም ለውጥ በመጣበት ሁኔታ ውስጥ እነ ፕሮፌሰር መሥፍን በመንግሥት ደረጃ ትልቅ የሰብዓዊ መብት ጥሰት እንደሚፈፀም አድርገው በተቃዋሚ ፖርቲዎቻቸውና በተቋሞቻቸው አማካይት እነሱው በሚረዷቸው የግል መጽሄትና ጋዜጦች አማካይነት ሲያጋግሙት ቆዩ፡፡

ዲፕሎማቶችንና የውጪ ሚዲያዎችን በመጠቀም በውጪ ኃይሎች ገንዘብ በመታገዝ ሲያካሂዱት የኖሩትና እያካሄዱ ያሉት ጥላሸት የመቀባትና የማጥላላት፣

ስም የማጥፋት፣ የአትነሳም ወይ ዘመቻ በቀጥታ ሕዝቡንና ትውልዱን ወኔ ቢስ፤ ድንቁርና ያሸመደመደው፤ በተልካሻ ነገሮች የሚደለል፤ በጉልበት ለሚረግጠው ካልሆነ አዲስ አስተሳሰብ የማይጥመው ወዘተ…ቅስቀሳው ዙሪያ ጥምጥም ሲቋጭ የእነ ፕሮፌሰር መሥፍንና የአጋፋሪዎቻቸው ፖለቲካዊ ግብና ዓላማ በአክራሪ ኒዮ ሊበራል ፖለቲካል ኢኮኖሚ የሚመራ ኃይል፣ ስብስብ ወይንም ቡድን በኢትዮጵያ ሥልጣን እንዲጨብጥ ማድረግ ነው፡፡

ይህንን ለማሳካት ይቻል ዘንድ ረዥም ጊዜ በኢትዮጵያ የነበሩ የሲቪክ ማህበራትን ጥምረት በመፍጠር የሙያ ማህበራትን በማሰባሰብ ቅንጅት የሚል ስም በመስጠት መርተዋል፡፡ ይህን ለማሳካት 74 ሚሊዮን ብር በተለያየ መልኩ አውጥተዋል፡፡ በመጨረሻም በሽንፈት በውድቀት ታሪካቸው ተደምድሟል፡፡ ያ ሁሉ የተጠራቀመ ብሶት፣ ንዴት፣ ብስጭትና መትከንከን ነው ዛሬ ፕሮፌሰር መሥፍንን የለየላቸው ዘርጣጭና ተሳዳቢ ያደረጋቸው፡፡ አሁንም እንዲህ ተሳድቤ የዘጠቀ፣ የነፈዘ፣ ወኔ ቢስ፣ አቅመ ቢስ፣ ለሆዱ ያደረ ብዬ እንዲነሳ አድርገዋለሁ ብለው ማሰባቸው ራሱን ችሎ አስገራሚ ነው፡፡

ይልቁንስ በእሳቸው እድሜ ይገባ የነበረው ተተኪው ትውልድ በአስተዋይነትና በመቻቻልና በመግባባት፣ ችግሮችን በውይይት የመፍታት ባሕሉን አጠናክሮ እንዲይዝ ማስተማር ነበረ እንጂ ለጥፋት፣ ለሁከትና ለአመፅ እንዲነሳሳ ያለማቋረጥ መቀስቀስ መሆን አልነበረበትም፡፡ የትናንቱ በ1997 የቀሰቀሱት ግርግርና አመፅ ያስከተለው ጥፋት አልበቃ ብሏቸው ዘንድሮ በ2007 ያንኑ የቀለም አብዮት በሌላ ዘዴና ሥልት በኢትዮጵያ እንደግማለን ብለው ያላሴሩት ሴራ፣ ያልቀየሱት አዲስ ሥልት፣ እቅድና ስትራቴጂ የለም፡፡

አዛውንቱ ፕሮፌሰር በቀንደኛ አመጽ ቀስቃሽነት በፋክት መጽሄት አምደኝነት ያልፃፉት የተነሳ የአመፅ፤ የሩዋንዳው በኢትዮጵያ ይደገማል ወዘተ…የቅስቅሳ ጥሪ የቀራቸው ነገር የለም፡፡ ከላይ እንደተገለፀው በላኤ ሰብ በግዕዙ፤ በአማርኛው ሰው በላ የሚለው አገላለጽ የሚመጥነው ለራሳቸው ለፕሮፌሰሩ ነው፡፡ ከግለሰብም በላይ ሀገርን ለመብላት፣ ለማስበላት፤ እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል ባለችው እንሰሳ ተምሣሌነት ትውልድም ሀገርም ይገፍ ልጥፋ ብለው በጨለማ ፍልስፍና ውስጥ የሚናውዙ ግለሰብ ናቸው፡፡

ፕሮፌሰር መሥፍን ወልደማርያም በማይረባ ነገር የሚደለል፣ ወኔ ቢስ፣ ለሆዱ ያደረ ሲሉ ትውልዱን ይዘልፋሉ፡፡ መልእዕታቸውን አልሰማም ስላለ ነው፡፡ እውነቱን እንጋገር ከተባለ ከንጉሱ ጊዜ ጀምሮ በደርግና ዛሬም በዶላር እየተገዛ፣ እየተደለለ፣ ለነጮች ፍላጎት እያጐበደደና እያሸበረከ፣ ለዓላማቸው መሳካት ተላላኪና ቅጥረኛ ሆኖ ያደረ ከእሳቸው በላይ ማንም የለም፡፡ ጥንትም ባህላችን ለነጮች እንድንበረከክ አይፈቅድልንም፡፡

ወጊዱ ያላለ ወኔ ቢስ፣ ሐሞቱ የፈሰሰበት፣ ለሆዱ ያደረ የባዕዳን አገልጋይ ከፕሮፌሰር መሥፍን ወልደማርያም በላይ ማን አለ - ማንም የለም፡፡ ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም ስለ ፕሮሰር መሥፍን የውጭ አገልጋይነት በመናገራቸው ነው እሱን አትሰሙት፣ እብድ ነው የሚሉት፡፡

በአጭሩ በራሳቸው ቋንቋ ለመጠቀም የኢትዮጵያ ታሪክ በታላቅ ሕዳሴ ውስጥ ሲሆን እሳቸውም አስተሳሰባቸውም የከሸፈ፤ ከክሽፈት በስተቀርም አንዲትም የስኬትና የተሀድሶ ታሪክ የሌለው መና መሆኑን ሊረዱት ይገባል፡፡ የጂኦግራፊ መምህርና ፕሮፌሰር መሆን የፖለቲካል ሣይንስ ፕሮፌሰር መሆን ብቻውን የዓለምን እውቀት በሙሉ የጨበጥኩ ነኝ አስብሎ አያወናጭፍም፡፡

የዓለምን ታላላቅ የፖለቲካ ለውጦችና አብዮቶች የመሩት ግለሰቦች የኅብረተሰባቸውን ተጨባጭ እውነታ የተረዱ፤ ሕዝባቸውን ያከበሩ፤ ኑሮውን የኖሩ፤ ችግሩን የተቸገሩ፤ ረሐቡን የተራቡ ሞቱንም የሞቱለት በዚህም ውስጥ አልፈው የሚመጥነውን የትግል ሥልት የተከተሉ፤ ለሀገራቸውም የሚበጀውን ዓይነት የፖለቲካና የኢኮኖሚ ለውጥ ያመጡ እንጂ የግድ ፕሮፌሰር፣ ዶክተር፣ ኢንጂነር የነበሩ የሆኑ ሕዝባቸውን የሚሳደቡ፣ የሚዘልፉ፣ የሚንቁ፣ በእብሪት የታጀሉ ሰዎች አልነበሩም፡፡

ስለዚህም ፕሮፌሰር መሥፍንና መሰሎቻቸው ለ2007 የቀለም አብዮት የቀመሩት የሴራ ቀመር ዓይናቸው እያየ እንዳልሆነ ሆኖ ሕልማቸው መክኖ ሲቀር፤ ጤዛና ጉም ሆኖ ሲተንና ሲቦን እያዩት ነው፡፡

በፕሮፌሰሩ፣ በኢንጂነሩና በዶክተሩ የእብደት መናወዝ ከመገረም ውጪ አብሮ የሚደልቅ ሕዝብ የለም፡፡ በአክራሪ የኒዮ ሊበራል ኃይሎች የገንዘብ ድጐማ

የሰከሩትና እያሴሩ ያሉት እነዚሁ ወገኖች ሕዝብን መሳደቡን መናቁን እኛን የግድ ካልተከተለ ብለው ፀጉር መንጨታቸው የወድቀታቸው ታላቅ ምልክት ስለሆነ አያስገርምም፡፡